
ከድኅነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተሳሰፍ
2ኛ ዙር ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 2

# ጠና አበረ

## በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት



የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ)



ከድህነት ወደ ልማት፡- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ
2ኛ ዙር፡ ተከታታይ ዕትም፣ ቁጥር 2

# በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት

*ጠና አበረ*

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
አዲስ አበባ

© ነሐሴ 1999 የደራሲውና የማኅበራዊ ጥናት መድረክ

በአዲስ አበባ የታተመ

የሽፋንና የገጽ ዲዛይን:- በምህረት ደምሰው

ISBN-10: 99944-50-12-3
ISBN-13: 978-99944-50-12-1

**አድራሻ:**

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ
ፖ.ሣ.ቁ. 25864 ኮድ 1000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ስልክ: (251-11) 157-2990/91
ፋክስ: (251-11) 157-2979
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et
ድረ-ገጽ: www.fssethiopia.org.et

ይህ ጽሑፍ የታተመው ከኖርዌይ ኤምባሲ፣ ከኔዘርላንድስ ኤምባሲ፣ ከአየርላንድ ኤምባሲና ከእንግሊዝ ዓለም-አቀፍ የተራድኦ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው::

በዚህ ሕትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የማጥመን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን ወይም የማጥመን አጋሮች አመለካከት ሳያንፀባርቁ ይችላሉ::

**ማውጫ**

የመክፈቻ ንግግር
*ሺፈራው በቀለ*.............................................................................................................. *i*

**1. መግቢያ**.........................................................................................................***1***

**2. የወባ በሽታ የሥርጭት ሁኔታ**.............................................................................4

**3. የኢትዮጵያ የወባ ማጥፊያ ድርጅት መቋቋም**...................................................7

**4. የወቅቱ የኢትዮጵያ የወባ ሁኔታ**.....................................................................21

**5. የወባ በሽታ የወደፊቱ ስጋት**............................................................................22

**6. የኢትዮጵያ የወባ መቆጣጠሪያ ባለሙያዎች ማኅበር መቋቋም**...............24

# በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ሂደት፣ ነባራዊ ሁኔታና የወደፊቱ ስጋት

*ጠና አበረ*

## 1. መግቢያ

ዛሬ በዓለም ላይ ያለው የጤና አገልግሎት ሲታይ በጣም የተዛባ ነው:: የበለጸጉ አገሮች በተለይም ተላላፊ በሽታዎችንና ሌሎችንም የጤና ጠንቆችን በቁጥጥር ስር በማዋል የሕዝባቸውን ጤንነት በመጠበቅ የኑሮ ደረጃውን በይበልጥ እያሻሻሉ ናቸው:: በመልማት ላይ ያሉ የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች ግን ካለባቸው የድህነት ጫና በተጨማሪ ለበርካታ ተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ በመሆናቸው የኑሮ ደረጃቸው በየጊዜው እያሽቆለቆለ ይገኛል:: በዚህ ሳቢያ ነፍሰጡሯ ሳትገላገል፣ ጨቅላው ሳያድግ፣ ወጣቱ ሳይጐለምስ፣ ጐልማሳው ሳይሸመግል እንደቅጠል እየረገፈ ነው:: ለምሳሌ በታዳጊው ክፍለ ዓለም ከሚገኙት የጤና ጠንቆች መካከል የወባ በሽታ አንጋፋና በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ ነው::

### *1.1 የወባ በሽታ መሠረታዊ ዕውነታዎች*

ወባ በቀይ ደም ወይም በጉበት ውስጥ በጥገኝነት የሚኖሩ፣ የሚያድጉና የሚራቡ፣ በአጉሊ መነፅር (ማይክሮስኮፕ) ካልሆነ በስተቀር በዓይን የማይታዩ እና በእጅ የማይዳሰሱ፣ ኘላስሞድየም በመባል በሚታወቁ ረቂቅ ተህዋስያን አማካይነት የሚመጣ በሽታ ነው:: የወባ በሽታ በአንዳንድ አካባቢዎች ንዳድ በመባል ይታወቃል:: በተፈጥሮ በሰው አካል ውስጥ በመራባትና በማደግ ለበሽታው የሚያጋልጡት አራት የወባ ተህዋስያን ዝርያዎች ናቸው:: እነሱም:-

- ኘላስሞዲየም ፋልሲፓረም
- ኘላስሞዲየም ቫይቫክስ
- ኘላስሞዲየም ማላሪዬ
- ኘላስሞዲየም ኦቫሌ ይባላሉ::

ተህዋስያኑ ያላቸው ቅርጽ፣ እድገት፣ የትውልድ ብዛት፣ ለመራባት የሚወስዱት የጊዜ ፍጆታ፣ የበሽታው የጥቃት መጠን፣ በሰው ላይ የሚያሳዩት የግርሻ አይነትና ወቅት በመድኃኒቶች የመጠቃት ዝንባሌ፣ በአካል ውስጥ የሚያደርሱት የጉዳት ዓይነት የተለያየ ነው:: ከነዚሁ የወባ ተህዋስያን ዝርያዎች መካከል በሃገራችን በዋናነት በህብረተሰቡ ላይ ጥቃት የሚያደርሱት ኘላስሞዲየም ፋልሲፓረምና ኘላስሞዲየም ቫይቫክስ የሚባሉት ናቸው::

የወባ በሽታ የሚያስከትላቸው የጤና ጠንቆች በርካታ ናቸው:: ለምሳሌ የቀይ ደም ህዋሳትን በማጥቃት ለደም ማነስ የሚያጋልጥ ሲሆን፣ የአእምሮ መዳከም፣ ለጉበትና፣ ለኩላሊት መታወክ፣ እና በአጠቃላይ ለአካል ጉስቁልናና ለሞት ሊያጋልጥ ይችላል:: በተለይም ፕላስሞዲየም ፋልሲፓረም የተባለው የወባ ዝርያ በወቅቱ ተገቢው ሕክምና ካልተሰጠ በስተቀር ለሞት አደጋ ያጋልጣል:: የወባ በሽታ በተለይ ነፍሰጡር ሴቶችንና እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆነ ህፃናትን በይበልጥ የሚያጠቃ ሲሆን በቀላሉ ለአካል ጉስቁልናና ለሞት አደጋ ጭምር ያጋልጣል:: በተለይም አሁን ኤች አይ ቪ ኤድስ እየተስፋፋ በሄደበት ወቅትና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እየተጠናከረ በሚታየበት፣ እንዲሁም ከፍተኛ የምግብ ማነስና ያለመመጣጠን ችግር በሚታይበት ሁኔታ የወባ በሽታ ከምንግዜውም የበለጠ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሞት አደጋ ሊያጋልጥ እንደሚችል የጥናት መረጃዎች ይጠቁማሉ::

## *1.2 የወባ በሽታ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች*

- በሽተኛው ህመም ሲጀምረው ብርድ ብርድ የማለትና የማንቀጥቀጥ ስሜት ይከሰታል፣
- ጥርስ ማፋጨትና የሰውነት መወራጨት፣
- ጥቂት ቆይቶ የትኩሳትና የላብ መከሰት፣
- የምግብ ፍላጐት ያለመኖርና ቢመገቡም ማስመለስ፣
- ራስ ምታትና ውሃ ጥማት፣
- በጀርባና በአካል መገጣጠሚያዎች የቁርጥማት ስሜት መኖርና የመሳሰሉት ናቸው::

የወባ በሽታ ስሜቶችና መለያ ምልክቶች የወባ ተህዋስያን በቀይ ደም ህዋሳት ውስጥ የሚያደርጉትን የዕድገትና የመራባት ኡደት ከጨረሱ በኂላ በመጨረሻ ከቀይ ደም ህዋሳት ውሰጥ በመውጣትና በመስራጨት ሌሎች ጤነኛ የደም ህዋሳትን በሚያጠቁበት ጊዜ የሚከሰቱ ናቸው:: አንድ ሰው በወባ በሽታ በሚያዝበት ጊዜ ወዲያውኑ ተመርምሮ አስፈላጊውን ሕክምና ካላገኘ በስተቀር እንደወባው ዝርያ የሚለያይ ቢሆንም በየሁለትና ሶስት ቀናት ያገረሻል:: የወባ በሽታ በደም ህዋሳት ላይ በሚያደርሰው ጥቃት ከሚከሰቱት ምልክቶች በተጨማሪ :-

- ደም ማነስ
- መገርጣት
- ክብደት መቀነስ
- የጣፊያ እብጠት እና የመሳሰሉት አዘወትረው የሚታዩ ምልክቶች ናቸው::

## *1.3 የወባ በሽታ የመተላለፊያ መንገድ*

*በአገራችን ከግንዛቤ ማነስና፣ ከእምነት መዛባት የተነሣ የወባ በሽታ የበቆሎ አገዳና እሸት በመብላት እንደሚተላለፍ በአንዳንድ ቦታ ይታመናል:: ሆኖም ለዚህ ግምት መነሻው የበቆሎ አበባ በትንኝ መራቢያ ቦታዎች ላይ በሚረግፍበት ጊዜ ዕጮች በምግብነት ስለሚጠቀሙበትና የትንኝ ብዛት ስለሚጨምር ነው::*

*የወባ በሽታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፈው አነፎለስ በመባል በምትታወቀው እንስት የወባ አስተላላፊ ትንኝ አማካኝነት ብቻ ነው:: ትንኞች ሁሉ የወባ በሽታን የማያስተላለፉ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የወባ በሽታ አስተላላፊ የሆነችው ትንኝ የምትጥለውን እንቁላል ለማዳበር ደም መመገብ ስለሚያስፈልጋት በአጋጣሚ የወባ በሽታ ያለበትን ግለሰብ ደም ስትመጥ በደሙ ውስጥ የሚገኙት የወባ በሽታ ተህዋስያን በትንኟ ሆድ ውስጥ ከ10-12 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በማደግ ቅርፃቸውን በመለዋወጥ ይራባሉ::*

*ከዚያም በኋላ ትንኟ እንደገና ደም ለመመገብ ጤነኛን ሰው ስትነክስ የምትመጠው ደም እንዳይጓጉል (እንዳይረጋ) በመጀመሪያ ምራቋን በምትረጭበት ጊዜ ጥገኛ ተህዋስያኑም ከትንኟ የምራቅ ዕጢ ውስጥ ተቀላቅለው ከበሽተኛው ወደ ጤነኛው ሰው ይተላለፋሉ::*

*በጤነኛ ሰው ደም ውስጥ ትንኟ ጥገኛ ተህዋስያኑን ስትተፋ ወዲያውኑ ህመም አይሰማም:: ህመምተኛው ምንም ዓይነት ስሜት ሳይሰማው የተለመደ ተግባሩን እያከናወነ ከ10-14 ቀናት ደህና ሆኖ ሊሰነብት ይችላል:: በነዚህ ቀናት ውሰጥ በጉበቱ ውሰጥ ተህዋስያኑ ገብተው ይራባሉ:: ተህዋስያኑ እድገታቸውን ጨርሰው ከጉበት ውሰጥ በመውጣት ወደ ደም ቧንቧ በመሠራጨት ቀይ የደም ህዋሳትን ይወራሉ:: ይህም ክስተት በአራቱም የወባ ዝርያዎች የተለያየ ጊዜና ባህሪ ይኖረዋል:: ይህም የወባ በሽታ የመደላደያ ጊዜ ይባላል::*

*የወባ አስተላላፊ ትንኝ የምትራባው በአብዛኛው ከዝናብ ወራት በኋላ በየአካባቢው ተጠራቅሞ በሚቆይ ውሃ ውስጥ ነው:: እንቁላሎቹ በውሃው ላይ ወደ እጭ ከተለወጡ በኋላ እድገታቸውን ሲጨርሱ ትንኞች በመሆን ከውሃው ላይ በረው ይሄዳሉ:: የወባ ትንኝ ከመራቢያ ቦታዎች እስከ ሁለት ኪ.ሜ በመብረር ሰውን ለመንደፍ ትችላለች:: የወባ ትንኝ ደም ለመመገብ የምትንቀሳቀሰው በምሽትና በሌሊት ወቅት ብቻ ነው::*

## *1.4 የወባ በሽታ የመቆጣጠሪያ ዘዴዎች*

*የወባ በሽታ አስተላላፊ ትንኞች የሚራቡት በውሃ ውስጥ በመሆኑ በሰዎች መኖሪያ አቅራቢያ የሚገኙትንና በጊዜያዊነት የሚፈጠሩትን የውሃ ኩሬዎች የአካባቢ ቁጥጥር በማድረግ ማድረቅ ወይም ማዳፈን፣ ወይም ያቆረ ውሃ ካለ ቦይ በመቅደድ ማፋሰስ ይቻላል:: ትንኞት እንዳይራቡ ለማድረግ የአካባቢ ቁጥጥር በሚደረግበት ጊዜ የትንኞች*

*መፈልፈያ የሆኑና አገልግሎት የማይሰጡ ሰው ሰራሽና የተጠፈጥሮ ጉድጓዶችን መሙላትና ማስተካከል፣ ረግረጋማ ቦታዎችን ቦይ በመቅደድ ውሃውን ማፋሰስ፣ ውሃ የሚመጡ እንደ ባህር ዛፍ የመሳሰሉ ተክሎችን መትከል፣ በደረቃማ ወራት የተቆራረጡና ኩሬ የፈጠሩ ወንዞችን በመጥረግ በፍጥነት እንዲፈሱ ማድረግ፣ የመስኖ አርጅኖችን መጥረግና ውስጣቸው የበቀሉ ሳሮችን ማጨድና ውሃውን ማፋሰስ፣ በቤት ውስጥና ውጭ የሚገኙ ውሃ የሚያቁቱ እንደ እንስራ፣ በርሜሎች ቢርካና ጉድጓዶችን መክደን፣ በቤቶች ዙሪያ የተጣሉ አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ውሃ አቁረው የሚይዙ ሰባራ ቁሳቁሶችን ማስወገድ ያስፈልጋል።*


*ሌላው የመከላከያ እምርጃ ደግሞ፣ ሰፋፊ የውሃ ኩሬዎች ውስጥ የሚያድጉ እጮችን ለመግደል የወባ ባለሙያዎችን በማማከር የጸረ እጭ ኬሚካሎችን መርጨትና የተጠቃጠለ ዘይት በውሃ ላይ በማፍሰስ እጮቹ ታፍነው እንዲሞቱ ማድረግ ይቻላል። ይሁን እና ሊወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄና ሊያደርስ ስለሚችለው ጉዳት ምንጊዜም ቢሆን የባለሙያ ምክር መጠየቅ ወሳኝነት አለው።*

*የወባ ትንኝን ለመከላከል ዋንኛው ዘዴ የጸረ ትንኝ ኬሚካል (ዲዲቲ) መርጨት ስለሆነ ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤቶችን ለመርጨት በሚመጡበት ጊዜ ነዋሪዎች ሁሉ በፈቃደኛነት ቤታቸውን ማስረጨት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ በነፍስ ወከፍ ወይም በቤተሰብ ደረጃ በመድኃኒት የተነከረ የትንኝ መከላከያ አጐበር በአግባቡ መጠቀም ሌላው አማራጭ ነው። ይሁን እንጂ ስለወባ ትንኝ መከላከያ አጐበር አጠቃቀም ከጤና ባለሙያዎች ተገቢውን ምክር ማግኘትና አዘውትሮ ተግባራዊ ማድረግ ይመረጣል። ከሁሉም በላይ አንድ ሰው ወባማ በሆነ አካባቢ በሚታመምበት ጊዜ በፍጥነት በአቅራቢያ ወደሚገኝ የጤና ድርጅት ወስዶ ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል።*

## 2. የወባ በሽታ የሥርጭት ሁኔታ

### *2.1 የወባ በሽታ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ*

*የወባ በሽታ በሃገራችን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክፍለ አህጉራትና ክፍለ ሃገራት ተሰራጭቶ የሚገኝ በሽታ ነው። ለምሳሌ በአማካይ 107 አገሮችና አጎራባቾቻቸው ወባማ ናቸው። 40% (2.4 ቢሊዮን) የሚሆነው የዓለም ህዝብ ለወባ በሽታ የተጋለጠ ነው፣ ከ300-500 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በየዓመቱ በወባ በሽታ እየተጠቃ ነው፣ 2.7 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በየዓመቱ በወባ በሽታ ምክንያት ይሞታል፣ በእያንዳንዱ ሰከንድ ውስጥ 10 ሰዎች በወባ በሽታ ይያዛሉ፣ ነፍሰ ጡር ሴቶችና እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆነ ህፃናት እንዲሁም በምግብ ማነስና ያለመመጣጠን በሽታ የተጠቁ ግለሰቦች በይበልጥ በወባ በሽታ ተጠቂ ናቸው።*




የወባ በሽታን ዓለም አቀፍ ሥርጭት የሚያሳይ ካርታ

## *2.2 የአፍሪካ የወባ በሽታ ሁኔታ*

በመሠረቱ የወባ በሽታ ከድህነት ጋር የተቆራኘ ነው:: የአፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይም በስተደቡብ የሚገኙት ሃገራት በአብዛኛው ድሆች ናቸው:: በመሆኑም በአፍሪካ ውስጥ ከሚከሰተው የወባ በሽታ የሥርጭትና የሞት መጠን 90% የሚሆነው ከሰሃራ በታች በሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ነው፣ በየዓመቱ 1 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ በወባ በሽታ ምክንያት ይሞታል:: ከሚሞተው አንድ ሚሊዮን ሕዝብ መካከል 25% የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ናቸው:: አፍሪካ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በወባ በሽታ ምክንያት በየዓመቱ 12 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኪሳራ እየደረሰባት ነው፣

## *2.3 የኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪካዊ ገጽታ*

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከሚገኙት ሃገሮች መካከል በድህነትና በኋላ ቀርነት በግንባር ቀደምነት የምትጠቀስ ሃገር ናት:: የዚህም ዋናው ምክንያት በየጊዜው የሚከሰተው የምግብ እጥረት (ረሃብ)፣ ከፍተኛ የተላላፊ በሽታዎች ጥቃት በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ ናቸው:: የወባ በሽታ ደግሞ በሃገራችን ዘመን ያስቆጠረ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ ችግር መሆኑ ይታወቃል::

የኢትዮጵያ የወባ በሽታ ታሪክ በርካታ ምዕተ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በ17ኛውና በ18ኛው ክፍለ ዘመን (በዘመነ መሳፍንት) ከፍተኛ ረሃብና ወረርሽኝ አዘውትሮ ይከሰት እንደነበር የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ (የኢትዮጵያ ፍትሐነገስት)::

የችግሩ መንስዔ በውል ባልታወቀበት ሁኔታ የኢንፍሉዌንዛ፣ የወረርሽኝ በሽታ እየተባለ ይነገርለት ነበር:: ሳይንሳዊ የምርምር ሂደቶች እየተጠናከሩ በሄዱ ቁጥር የዚህ አደጋ ዋናው መንስኤ የወባ በሽታ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ::

## *2.4 በኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታ የዘመናዊ ጥናት አጀማመር*

- በኢትዮጵያ ውስጥ በሳይንስ የተደገፈ የወባ በሽታ የምርምር ጥናት የተጀመረው በጣሊያን ወረራ ጊዜ ነው፣
- ከ1929-1934 የጣሊያን ዜጎች ለመጀመሪያ ጊዜ በወባ በሽታ ላይ የአሰሳ ጥናት አደረጉ፣
- በ1938፣ 1945፣ 1948 ተጨማሪ የአሰሳ ጥናት በእንግሊዞች ተካሄደ፣ በተለይም በሰር ጉርደን ኮቬል (Sir Gordon Covel)
- በ1946፣ 1948 በጐንደር፣ በጣናና በባህርዳር አካባቢ በወባ በሽታ ምክንያት በርካታ ሰዎች እንደተጎዱ ጥናታዊ ዘገባዎች ያስረዳሉ፣
- ከ1948-1950 በኢትዮጵያ ውስጥ ዲዲቲ የተባለውን ጸረተባይ ኬሚካል በመጠቀም በወባ በሽታ ላይ የሙከራ ጥናት (Pilot Project) ተደረገ፣

የሙከራ ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግ ለወባ በሽታ ተጠቂ በሆኑት በተመረጡ አካባቢዎች ማለትም:-

- በአዋሽ ሸለቆ - (በዓለም ጤና ድርጅትና በዩኒሴፍ ድጋፍ)
- በቆቦ - ጨርጨር
- በወሎ - ደንቢያ
- በጐንደር እና በጋምቤላ ቀደም ሲል ፖይንት ፎር ሲባል በነበረው ዛሬ (ዩኤስ ኤይድ እየተባለ በሚጠራው የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት ድጋፍ የሙከራ ጥናት (Pilot Project) ተካሄደ::

በወባ በሽታ ላይ የሙከራ ጥናት በተደረገበት ጊዜ አንዳንድ መሠረታዊ ተግባራት ተከናውነዋል::

እነርሱም:-

- በከፍተኛ ደረጃ ወባማ የሆኑትን አካባቢዎች ካርታ በማንሳት መለየት፣
- የትንኝ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣
- የደም ናሙና መሰብሰብ፣ ደም መመርመርና ለወባ በሽታ ለተጋለጡ ህሙማን መድኃኒት መስጠት፣
- የመኖሪያ ቤቶችን ዲዲቲ በተባለው ጸረ ወባ ትንኝ መድኃኒት መርጨትና የመሳሰሉት ናቸው::

የሙከራ ጥናቱን (Pilot Project) ተግባራዊ ለማድረግ በተመረጡ ስፍራዎች ንኡስ ጣቢያዎች ተቋቁመው ነበር::
እነርሱም:-

- አዘዞ ንዑስ ጣቢያ - በጐንደር ክፍለ ሃገር

- *አላማጣ ንዑስ ጣቢያ - በወሎ ክፍለ ሃገር*
- *ባህርዳር ንዑስ ጣቢያ- በጐጃም ክፍለ ሃገር*
- *ጋምቤላ ንዑስ ጣቢያ- በኢሉባቦር ክፍለ ሃገር*
- *ኮምቦልቻ ንዑስ ጣቢያ- በወሎ ክፍለ ሃገር*
- *ናዝሬት ንዑስ ጣቢያ-በሸዋ ክፍለ ሃገር ነበሩ፡፡*

*የሙከራ ጥናቱም ዲዲቲ የተባለውን ጸረ ትንኝ መድኃኒት በመኖሪያ ቤቶች ውሰጥ በመርጨት በተደረገው ሙከራ የወባ በሽታን ስርጭት በመቀነስ ረገድ መልካም ውጤት አስገኝቶ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በ1958 ዓ.ም ታላቁ የወባ ወረርሽ በሀገራችን ተከሰተ፡፡ በወረርሽኙ ምክንያት በስድስት ወራት ብቻ* 3,000,000 *ሕዝብ (በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር 15% የሚሆነው) በወረርሽኙ የተጠቃ ሲሆን 150.000 (በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር 5% የሚሆነው) ለሞት አደጋ የተጋለጠበት ወቅት ነበር፡፡*

## 3. የኢትዮጵያ የወባ ማጥፊያ ድርጅት መቋቋም



*የመጀመሪያው የወባ ማጥፊያ ድርጅት ዋና መ/ቤት*

*ለኢትየጵያ ወባ ማጥፊያ ድርጅት መቋቋም ምክንያት ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡-*

- *ከፍ ሲል እንደተገለጸው የተደረገው የሙከራ ጥናት ውጤታማ በመሆኑ፣*
- *የተከሰተው ታላቁ የወባ ወረርሽኝ ያስከተለው አደጋ ከምንጊዜውም በላይ አሰቃቂ በመሆኑ፣*
- *በዘመኑ በሌላው የዓለም ክፍል ጭምር ወባን የማጥፋት ዘመቻ የተፋፋመበት ወቅት በመሆኑ፣*

- *ዓለም አቀፍ አጋሮቻችን የወባ በሽታን ለማጥፋት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ሁለገብ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ ሆነው በመገኘ ታቸው፣*
- *የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥትም የወባ ማጥፊያ ኘሮግራም በሃገራችን እንዲቋቋም ፈቃደኛ በመሆኑ፣ የካቲት 21 ቀን 1951 ዓ.ም የወባ ማጥፊያ ድርጅት በኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግሥት ትዕዛዝ ቁጥር 22 በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ስር እራሱን ችሎ ተቋቋመ::*



የወባ ማጥፊያ ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረው
የወባ በሽታ ሥርጭት ሁኔታ የሚያሳይ ካርታ

## *3.1 የወባ ማጥፊያ ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በኢትዮጵያ የነበረው የወባ በሽታ ሥርጭት ሁኔታ*

- *70% የሚሆነው የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ወባማ ነበር፤*
- *50% የሚሆነው ህዝብ ለወባ በሽታ የተጋለጠ ነበር፤*
- *በ1958 ዓ.ም ታላቁ የወባ ወረርሽኝ ተከሰተ፤*

ለምሳሌ የወባ ማጥፊያ ድርጅት በተቋቋመበት ጊዜ በወባ በሽታ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቁት አካባቢዎች አንዱ ሞጆና አካባቢው ነበር:: በመሆኑም በወቅቱ የተከሰተውን የወባ በሽታ አደገኛነት ለማንጸባረቅ ኅብረተሰቡ

- «ሞጆ አገሩ ቆንጆ ሬሳ አይጠፋም ከጉጆ» ይባል ነበር፤
- «የሞጆ ወባ ይገንድስህ!» እየተባለም የዕርግማን ቃል ይሰነዘር ነበር፤
- በወባ በሽታ ምክንያት ይደርስ በነበረው የአእምሮ ጉዳት የተነሳ «የቆላ ሰው ለምስክርነት አይበቃም» እየተባለ ይነገር ነበር::

## *3.2 ብሔራዊ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ማሰልጠኛ ት/ቤት መቋቋም*

በ1951 የወባ በሽታን ለማጥፋት አስፈላጊ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል ብሔራዊ የወባ ማሰልጠኛ ተቋም በናዝሬት ከተማ ተከፈተ::




በዚህ የማሠልጠኛ ማዕክል በርካታ:-


- የመስክ የኦፕሬሽንና የካርታ ሥራ ቴክኒሻኖች፣
- የትንኝ ጥናት ቴክኒሻኖች፣
- የደም ጥናት ቴክኒሻኖች (የላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች)፣
- የወባ በሽታ ደም መርማሪዎች (Microscopists )፣
- የጤና አጠባበቅና የህዝብ ግንኙነት ባለሙያዎች ሠልጥነው ተመርቀዋል::

የሰለጠኑት ባለሙያዎች በመስክ ሥራ በቂ ልምድ ካገኙ በኂላ ብቃት ያላቸው ተመርጠው የቴክኒኩን የመስክ ሥራ በኃላፊነት የሚመሩ ተቆጣጣሪዎች፣ በንኡስ ጣቢያ ደረጃ የአስተዳደሩን ሥራ በኃላፊነት የሚመሩ የንኡስ ጣቢያ ኃላፊዎች፣ የዋና መ/ቤቱንና የዓቢይ ጣቢያ ጽ/ቤቶችን በኃላፊነት የሚመሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች ወደ ውጭ አገር ተልከው ስልጠና ተሰጥቷቸዋል:: በአጠቃላይ የማሠልጠኛ ተቋሙ በሺህ የሚቆጠሩ ባለሙያዎችን አፍርቶ ነበር፣ በአሁኑ ጊዜ የማሰልጠኛ ተቋሙ የታጠፈ በመሆኑ ባለሙያዎችን በመደበኛነት ማሰልጠን ካቋረጠ ረጅም ጊዜ ሆኖታል::



## *3.3 የኢትዮጵያ የወባ ማጥፊያ ድርጅት የአስተዳደር መዋቅር*

### የኢትዮጵያ ን.ነ. መንግሥት በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
### የወባ ማጥፊያ ድርጅት



ይህን የመሰለ የተጠናከረ መዋቅር መኖር በአስተዳደርም ሆነ በቴክኒኩ አገልግሎት የሥራ ቅልጥፍናን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ ከመሆኑም በላይ መልካም የሥራ ውጤትም አስገኝቶ ነበር፡፡

### *3.4 የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ*

የወባ ማጥፊያ ድርጅት ሥራውን በይፋ የጀመረው ንጉሰ ነገስቱ መጋቢት 1 ቀን 19951 ዓ.ም በሰጡት መሪ ቃል ነበር፡፡ በወቅቱ የተላለፈውን መሪ ቃል ለግንዛቤ ያመች ዘንድ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡



ንጉሰ ነገስቱ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ሥራን በይፋ ሲያስጀምሩ

*« ..... የወባ ማጥፋት ሥራ የሕዝቡን ርዳታ የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ሕዝባችንም በሙሉ ልቡ ለዚህ ለተቀደሰ ሥራ ተባባሪ እንደሚሆን እምነት እንጥልበታለን፡፡ በተለይም ጠቅላይ ገዥዎች፣ እንደራሴዎች፣ የአውራጃና የወረዳ ገዥዎች፣ ባላባቶችና ምስለኔዎች፣ ጭቃሹሞች፣ የሕዝብ መሪ እንደመሆናቸው መጠን ከድርጅቱ ጋር በመተባበር ሕዝቡን እንዲያስተምሩና እንዲያበረታቱ እንዲያደርጉ አደራ የተጣለባቸው መሆኑን እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል፡፡*

*በአገራችን ወባን ለማጥፋት የሚደረገው ትግል ጥሩ ውጤት እያስገኘ መሄዱን አይተናል፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስትራችንና እናንተም የወባ ማጥፊያ ድርጅት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሕይወታችሁን ለወገናችሁ አገልግሎት ለማዋል ቆርጣችሁ ተነሥታችኋል፡፡ በሥራችሁ ብዙ ድካምና ፈተና እንደሚገጥማችሁ የታወቀ ነው፡፡ ቢሆንም የተቀበላችሁትን ኃላፊነት ተገንዝባችሁ ሐሳባችሁን ባለማዛባት ይህን የተቀደሰ ሥራ ፍጻሜ እንድታደርሱት ሁላችሁንም አደራ እንላችኋለን....እግዚአብሔር የተባረከ ሥራ ያድርገው»*

*መጋቢት 1 ቀን 19951 ዓ.ም*

## *3.5 የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ የጊዜ ሰሌዳ*

**በሃገራችን ታቅዶ የነበረው የወባ ማጥፊያ ድርጅት የሥራ እንቅስቀሴ በአራት የጊዜ ሰሌዳ የተከፈለ ነበር፡፡**

1. **የመዘጋጃ ጊዜ = 3 ዓመታት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ወቅት ፣ የካርታ ሥራ ዝግጅት ፣ ወባማ አካባቢዎችን መለየት፣ በተመረጡ አካባቢዎች የሚገኙ ቤቶች ሁሉ ካርታ እንዲነሱ ማድረግ፣ እና ለመኖሪያ ቤቶች ቁጥር መስጠት የት እንዳሉ የማወቅና የመሳሰሉት፡፡**

2. **የማጥቂያ ጊዜ = 4 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ወቅት የወባ ትንኞች የሚያርፉባቸው ቤቶች ሕንፃዎች ወይም ሌሎች መጠለያዎች ሁሉ የጸረ ትንኝ መድኃኒት በመጠቀም በአግባቡ ይረጫሉ፡፡**

3. **የማጠናከሪያ ጊዜ = 3 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ወቅት ወባ የሚተላለፍባቸውን ሥፍራዎች ለማወቅ የአሰሳ ጥናት ማድረግ፣ ለወባ በሽታ መንስዔ የሆኑትን ሁኔታዎች ሁሉ ማጥፋትና ይህ ወቅት ወባ በሽታ ተመልሶ እንዳያገረሽ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱ የሚረጋግጥበት ጊዜ ነው፣**

4. **የመጠባበቂያ ጊዜ = 7 ዓመት የሚፈጅ ሲሆን በዚህ ወቅት የወባ በሽታ ሙሉ በሙሉ ከጠፋ በኋላ ሥራውን ለመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ማስረከብ የታቀደበት ጊዜ ነው፡፡**

| 1 | 2 | | | 3 | | 4 | | 5 | | | 6 | | | 7 | 8 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዓ.ም. | 1956 - 1958 | | | 1959 - 1960 | | 1961 - 1962 | | 1963 - 1964 | | 1965 | 1966 - 1968 | | | 1969 | 1970 - 1972 | | | |
| አካባቢ | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ሀ | የመ | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ |
| ለ | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | |
| ሐ | | | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | የመቆ | የመቆ | |
| መ | | | | | | | | የመ | የመ | የማ | የማ | የማ | የማ | የማጠ | የማጠ | የማጠ | የመቆ | |

<u>**መፍቻ፡-**</u> **የመ = የመዘጋጃ ጊዜ**
**የማ= የማጥቂያ ጊዜ**
**የማጠ = የማጠናከሪያ ጊዜ**
**የመቆ = የመቆጣጠሪያ ጊዜ**

## 3.6 የወባ ማጥፊያ ድርጅት የመስክ ሥራ እንቅስቃሴ



የድርጅቱ ሠራተኞች በወባማ ሥፍራዎች እየተዘዋወሩ ወባማ ቀበሌዎችን ካርታ ሲያነሱ



ከየቀበሌው የተነሱ ካርታዎች ወደዋናው መ/ቤት ተልከው ሲባዙ



ባለሙያዎች ቤት በሚረጨበት ጊዜ ህብረተሰቡ የዲዲቲ መበጥበጫ ውሃ በማቅረብና የቤት ቁሳቁሶችን በማውጣት ሲተባበር



ለመርጨት አስቸጋሪ የሆኑ ባለሁለት ፎቅ ጎጆ ጭምር ሲረጭ



የመኖሪያ ቤት የውስጥ ክፍል ሲረጭ ትንኞች ወደ ውጭ ወጥተው እንዳያርፉ የቤቱ ተዛነብ ጭምር በዲዲቲ ሲረጭ



የድርጅቱ ሠራተኞች የመስክ ኑሮ




ከዋናው መ/ቤት ጋራዥ መኪናዎች በጥገና ላይ

ለመስክ ሥራ ዝግጁ የሆኑ ተሽከርካሪዎች



የመስክ ሠራተኞች በመኪና ሲጓዙ



የመስክ ሠራተኞች በባቡር ሲጓጓዙ



የመስክ ሠራተኞች በእግርና በጋማ ከብት ለበርካታ ቀናት ሲጓዙ



የመስክ ሠራተኞች በአውሮኘላን ሲጓዙ



የትንኝ ዕጭ ከኩሬ ውስጥ ለጥናት ሲሰበሰብ



የወባ አስተላላፊ ትንኝ ከቤት ውስጥ ሲለቀም



የወባ አስተላላፊ ትንኝ ዝርያዎችን ለመለየት በዋናው መ/ቤት በሚገኘው የትንኝ ጥናት ላብራቶር ምርመራ ሲደረግ



ሕመምተኞች ወደ ጤና ድርጅት መምጣት ሲሳናቸው የወባ በሽታ ህክምና አገልገሎት በመስክ ሲሰጥ



ህዝብ በሚሰበሰብባቸው ሥፍራዎች በባለሙያዎች ለህብረተሰቡ የጤና ትምህርት ሲሰጥ



ስለወባ በሽታ በሃይማኖት አባቶች ለህብረተሰቡ ትምህርት ሲሰጥ



ለተማሪዎችና ለሌላውም ህብረተሰብ ጭምር ስለወባ በሽታ የፊልም ትርኢት ሲታይ

### 3.7 የወባ ማጥፊያ ድርጅት የስራ እንቅስቃሴ ያስገኛቸው ውጤቶች

- በሙያ ዘርፉ በርካታ የሰለጠነ የሰው ኃይል አፍርቷል፣
- የተጠናከረ ድርጅታዊ መዋቅር ፈጥሯል፣
    - 1 ዋና መ/ቤት - በአዲስ አበባ
    - 14 አብይ ጣቢያዎች - በየክፍለ ሃገሩ
    - 5 መለስተኛ አብይ ጣቢያዎች (በተመረጡ ሥፍራዎች)
    - 50 ንዑሳን ጣቢያዎች በየአውራጃው
    - 20 የወባ ጤና ኬላዎች
    - በአጠቃላይ 80 የሚሆኑ የወባ ጤና ተቋማት ተቋቁመው የወባ በሽታን በማጥፋት ዘመቻ ላይ መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል፣
- ድርጅቱ በሰጠው አገልግሎት እንቅስቃሴ በተደረገባቸው በአካባቢ «ሀ» (A) ከ30-40% የነበረው የወባ በሽታ ጥቃት ወደ 5% እና ከዚያ በታች ዝቅ ብሎ ነበር፡፡ ይህ እርምጃ ባስገኘው ውጤት የወባ በሽታ የህብረተሰቡ አብይ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ችግር እንዳይሆን አድርጎት ነበር፡፡





በወባ በሽታ ፍራቻ ምክንያት ጠፍ ሆነው ቆይተው የነበሩ ለም መሬቶች

ከወባ በሽታ ነፃ በመሆናቸው የእርሻና የኢንዱስትሪ ምርት ማዕከል የሆኑ አካባቢዎች፡- ለምሳሌ

- የተንዳሆ የጥጥ እርሻ ልማት
- የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት
- የወንጂ ስኳር ፋብሪካ
- የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ
- የሁመራ እርሻ ልማት
- የመተማ እርሻ ልማት
- የባህርዳር ከተማ
- የደምቢያና ፎገራ አካባቢዎች እና ሌሎችም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

## *3.8 የወባ ማጥፊያ ድርጅት የአገልግሎት ሽፋን*



በሀገሪቱ የተቋቋሙ ዓቢይና ንዑሳን ጣቢያዎችን የሚያሳይ ካርታ

### *የአካባቢ ሀ ዓቢይ ጣቢያዎችና ንኡሳን ጣቢያዎች ስርጭት*

**1. አሥመራ ዓቢይ ጣቢያ**

- አዲኡግሪ ንዑስ ጣቢያ
- ከረን ንዑስ ጣቢያ
- ምጽዋ » »
- አቆርዳት » »
- ባሬንቱ » »
- ተሰነይ » »
- ሁመራ » »

**2. መቀሌ ዓቢይ ጣቢያ**

- መቀሌ ንዑስ ጣቢያ
- ተምቤን » »
- ሰቆጣ » »
- አድዋ » »
- ሽሬ እንዳስላሴ

**3. ጐንደር ዓቢይ ጣቢያ**

- አዲስ ዘመን ንዑስ ጣቢያ
- ደልሚ » »
- አዲአርቃይ » »
- አይከል » »
- ሁመራ » »
- ንፋስ መውጫ » »

**4. ደሴ (ኮምቦልቻ) ዓቢይ ጣቢያ**

- ከምቦልቻ ንዑስ ጣቢያ
- ሸዋ ሮቢት » »
- ወልዲያ » »
- አላማጣ » »

**5. ድሬዳዋ ዓቢይ ጣቢያ**

- ድሬዳዋ ንዑስ ጣቢያ
- ሐረር » »
- ደደር » »
- ሂርና » »
- ሚኤሶ » »
- በዴሳ » »
- በደኖ » »
- መቻራ » »

**6. ደብረዘይት ዓቢይ ጣቢያ**

- የመጀመሪያው ዓቢይ ጣቢያ
- ደብረዘይት ንዑስ ጣቢያ
- ናዝሬት » »
- አዋሽ » »
- አዲስ አለም » » (ወደ ኋላ ላይ ወደ ናዝሬት ዓቢይ ጣቢያ የተቀየረ)

**7. ደብረማርቆስ ዓቢይ ጣቢያ**

- ሞጣ ንዑስ ጣቢያ
- ደብረማርቆስ » »
- ቢቸና » »
- መተከል » »

## በአካባቢ «ለ» የተቋቋሙ ዓቢይና ንኡሳን ጣቢያዎች

**1. ነቀምቴ ዓቢይ ጣቢያ**

- ባኮ ንዑስ ጣቢያ
- ነቀምቴ ንዑስ ጣቢያ
- ጊምቢ » »
- ጊዳ አያና » »

**2. ደምቢ ደሎ ዓቢይ ጣቢያ**

- ጊዳሚ ንዑስ ጣቢያ
- ዓለም ተፈሪ » »
- አሶሳ » »
- ቤጊ » »

**3. አዋሳ ዓቢይ ጣቢያ**

- ያቤሎ ንዑስ ጣቢያ
- ዲላ ንዑስ ጣቢያ
- ሞያሌ » »
- አዋሳ » »
- ነጌሌ ቦረና » »
- አላባ ቁሊቶ » »
  አርባምንጭ (በኋላ ወደ ዓቢይ ጣቢያ ተለወጠ)

**4. ጅማ ዓቢይ ጣቢያ**

- ጅማ ንዑስ ጣቢያ
- ቡኖ በደሌ » »
- ጋምቤላ » »
- መቱ » »
- ቦንጋ » »

***ከ1959-1963 ዓ.ም የማጥቂያ ጊዜ በአካባቢ "ሀ" ተጀምሮ በተከታታይ በአካባቢ "ለ" ተግባራዊ እንዲሆን ታቅዶ ነበር። በአጠቃላይ የወባ ማጥፊያ ኘሮግራም በመላ ሃገሪቱ በ1980 ዓ.ም እንዲዳረስ ታስቦ ነበር። ይሁንና የወባ ማጥፋቱ ኘሮግራም በአካባቢ "ሐ" እና "መ" ተግባራዊ ሳይሆን ኘሮግራሙ ተቋረጠ።***

**የኢትዮጵያ ወባ ማጥፊያ ድርጅትን የመሩ ኃላፊዎች፦**

***አቶ ሠይፈሚካኤል ዘለቀ - የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዳይሬክተር***
***አቶ በቀለ ተገኝ 2ኛው ሥራ አስኪያጅ***
***አቶ አመሐ እሸቴ ሦስተኛው ሥራ አስኪያጅ***
***አቶ ኃይሉ መቼ አራተኛ ሥራ አስኪያጅ***
***አቶ ጥላሁን አበበ አምስተኛ ሥራ አስኪያጅ***
***አቶ የማነ ተከስተ ስድስተኛ ሥራ አስኪያጅ***
***ዶ/ር አዋሽ ተ/ሃይማኖት የመጨረሻው ሥራ አስኪያጅ ሲሆኑ ከዚያ በኋላ የወባ ማጥፊያ ድርጅት ወደ ወባ ቁጥጥር ኘሮግራም ተለወጠ።***

## *3.9 በወባ ማጥፊያ ድርጅት ላይ የተደረጉ መዋቅራዊ ለውጦች ያስከተሏቸው ችግሮች፡*

### *3.9.1 የወባ ማጥፊያ ድርጅት፡-*

በ1962 ዓ.ም በዓለም ጤና ድርጅት ውሳኔ መሠረትና ሃገራችንም ስለተቀበለችው የወባ ማጥፊያ ኘሮግራም ታጥፎ ወደ ወባ መቆጣጠሪያ ድርጅት ተቀየረ፡፡

### *3.9.2 የወባ መቆጣጠሪያ ድርጅት፡-*

ከ1972-1978 ዓ.ም የወባ መከላከያ ድርጅት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በጤና አገልግሎት መምሪያ ሥር የወባ መከላከያ ኘሮግራም በመባል በዋና ክፍልነት ዝቅ ብሎ በአዲስ መልክ ተዋቀረ ፡፡

### *3.9.3 የወባ መቆጣጠሪያና መከላከያ ኘሮግራም፡-*

ከ1972-1978 ዓ.ም የወባ መከላከያ ኘሮግራም ተባለ

### *3.9.4 የወባና ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች መከላከያ ድርጅት፡-*

ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ የወባ መከላከያ ኘሮግራም ወደ ብሔራዊ የወባና ሌሎች ቬክተር ወሊድ በሽታዎች መከላከያ ድርጅት ተባለ፡፡ አሁንም ቢሆን ድርጅቱ የሚጠራው የወባና ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች ቁጥጥር እየተባለ ነው፡፡ ሌሎች ቬክተር ወለድ በሽታዎች የሚባሉት

- ሽስቶሶሚያሲስ (ቢልሐርዚያ)
- ሆንክስርኪያሲ
- የዕንቅልፍ በሽታ
- ቆንጭር (ሌሽማኒያሲስ)
- የጊኒ ወርም እና
- የወባ በሽታ ናቸው፡፡

ድርጅቱ የወባ በሽታን ጨምሮ ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን ቬክተር ወለድ በሽታዎች ለመከላከል እቅድ ያወጣ ቢሆንም ቢልሐርዚያ በተሰኘ ው በሽታ ላይ አንዳንድ መሠረታዊ እንቅስቃሴዎች ከመደረጋቸው በስተቀር ተጨማሪ ሥራ ስለመከናወኑ የተዘገበ መረጃ የለም፡፡ ይልቁንም ድርጅቱ ከአቅሙ በላይ ተለጥጦ በመዋቀሩ የወባ በሽታንም የታሰበውን ያህል ለመከላከልም ሆነ ለመቆጣጠር ያስቻለ የሥራ እንቅስቃሴ አልነበረውም፡፡

በየጊዜው በተደረገው የመዋቅር ለውጥ ምክንያት አብዛኛዎቹ ዓቢይ ጣቢያዎችና ንኡስ ጣቢያዎች ተዘጉ:: የሠለጠኑ ከፍተኛና መለስተኛ ባለሙያዎች ተበተኑ:: የወባ በሽታን የመከላከል ወይም የመቆጣጠር እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ተዳከመ:: በዚህ ሳቢያ በተደጋጋሚ አገር አቀፍ የወባ ወረርሽኝ እንደገና የተከሰተ ሲሆን ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል::

በ*1966-67*፣ በ*1973-74*፣ በ*1983-84*፣ በ*1990-91*፣ *1996-97* በአገር አቀፍ ደረጃ የወባ ወረርሽኝ ተከስቶ ከፍተኛ የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ አስከትሏል:: በርካታ ሕይወትም ጠፍቷል:: በመሆኑም ይህ ሁኔታ ሲታይ በየአምስት ዓመቱ የወባ ወረርሽኝ ሊከሰት እንደሚችል የጥናት መረጃዎች ያመለክታሉ::

### 3.9.5 የወባ መከላከያ ድርጅት የውህደት ፕሮግራም

የወባ መከላከያ ድርጅት በየጊዜው በተደረጉት መዋቅራዊ ለውጦች የተዳከመ ቢሆንም የበሽታው የጤና፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ ቀውስ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከሌላው የጤና አገልግሎት ጋር በውህደት እንዲቀሳቀስ መደረጉ የሥራው እንቅስቃሴ የበለጠ እንዲዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ከሁሉም በላይ በጤና ድርጅቶች የሚገኙ ባለሙያዎች ስለወባ በሽታ መሠረታዊ ግንዛቤ እንዳላቸው የማይካድ ቢሆንም በተለይ ስለትንኝ ጥናት ስለሌሎችም የወባ በሽታ የመስክ የሥራ እንቅስቃሴዎች ሥልጠና ሳይሰጥ ኃላፊነቱን እንዲሸከሙ መደረጉ ካላቸው የሥራ ጫና ጋር ሊወጡት የማይችሉት ችግር ሆኖ በመገኘቱ የመስክ የሥራ እንቅስቃሴው ከሞላ ጉደል መቋረጡ የማይታበል ነው::

ከዚያም በላይ የተደረገው ድርጅታዊ ውህደት አካላዊ እንጅ ተግባራዊ ባለመሆኑ የድርጅቱን መዋቅር የሰው ኃይል የፋይናንስና የንብረት ምንጮችን እንዲዳከሙ አድርጓል:: በአጠቃላይ ሲታይ ያለበቂ ጥናት ወይም የመሸጋገሪያ ጊዜ ሳይሰጥ የተደረጉት ድርጅታዊ ለውጦች በፕሮግራሙ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰዋል::

### 3.9.6 ካልተማከለ የአስተዳደር መዋቅር (Decentralization) አኳያ የወባ መከላከያ ፕሮግራም ሲታይ

በመሠረቱ ያልተማከለ አስተዳደር በየአካባቢው መንደር አቀፍና ህብረተሰቡን ያሳተፈ የወባ በሽታ ቁጥጥር ሥራን ለማጠናከርና ውጤት ለማስመዝገብ ጭምር የተሻለ እርምጃ ነው:: በዚህ የአገልግሎት ዘርፍ ቀበሌዎችንና ወረዳዎችን በማጠናከር ተሳትፎውን ለማጎልበት አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል:: ነገር ግን የወባ በሽታ ቁጥጥር ሥራ ዘርፈ ብዙና የባለሙያ ድጋፍ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህ ባልተሟለበት ሁኔታ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚያስቸግር ከነባራዊ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል:: በመሆኑም:-

- በወባ ቁጥጥር ሥራ ላይ ያተኮረ ሥልጠና በማይሰጥበት በአሁኑ ጊዜ በወረዳ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማሟላት አስቸጋሪ በመሆኑ፣
- በየወረዳው የሚገኙ የጤና ባለሙያዎች (ሃኪሞች፣ ነርሶች፣ የአካባቢ ጤና ተቆጣጣሪዎች፣) ባላቸው ሙያ ላይ ስለወባ በሽታ የመስክ ሥራ በተለይም ስለወባ አስተላላፊ ትንኞች ተጨማሪ ግንዛቤ ማግኘት ስለሚያስፈልጋቸው፣
- በየቀበሌው የሚመደቡ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችም የቅርብ ቁጥጥርና ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው፣
- የወባ በሽታ ከሚያስከትለው መጠነ ሰፊ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመከላከልና የመቆጣጠር እርምጃ ለመውሰድ የበለጠ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የወባ በሽታ ከሚያስከትለው ጫና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የወባ ቁጥጥር ሥራ ለመውሰድ አስቸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል:: ስለዚህ በተለይ በየክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የበለጠ እንቅስቃሴ ቢደረግ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝ ይችላል::

## 4. የወቅቱ የኢትዮጵያ የወባ ሁኔታ

በሃገራችን በአጠቃላይ ካለፉት 47 ዓመታት ጀምሮ የወባ በሽታን ለማጥፋት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ዛሬም ቢሆን የወባ የሽታ:-

- ግንባር ቀደም የጤና ችግር፣
- ከፍተኛ የህመምና የሞት ምክንያት፣
- የጤና የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ቀውስ፣
- እንዲሁም ለድህነታችን ዋንኛ ምክንያት ሆኖአል::

በመሆኑም አሁን ባለንበት ወቅት ያለው የወባ በሽታ ሁኔታ ሲታይ:-

- 75% የሚሆነው የሀገሪቱ የቆዳ ስፋት በወባ ጥቃት ስር ወድቆ ይገኛል፣
- ከባህር ወለል በላይ እስከ 2000 ሜትር ድረስ ብቻ በሚገኙ አካባቢዎች ይደርስ የነበረው የበሽታው ጥቃት በአሁኑ ጊዜ እስከ 2300 ሜትር ድረስ እየተስፋፋ ነው፣
- በሀገራችን የወባ በሽታ ግንባር ቀደም የህመምና የሞት ምክንያት ነው፣
- በአማካይ ግምት 48 ሚሊዮን የሚሆነው ህዝብ (ከአጠቃላዩ የህዝብ ብዛት 65%) ለወባ በሽታ ጥቃት ተጋልጦ ይገኛል፣
- ለተመላላሽ ህክምና ወደ ጤና ድርጅት ከሚሄዱት ህሙማን መከካል 16% የሚሆኑት የወባ ህመምተኞች ናቸው፣

- *ታመው በሆስፒታል ከሚተኙት መካከል 20% የሚሆኑት የወባ በሽታ ተጠቂዎች ናቸው፣*
- *በሆስፒታል ተኝተው ከሚታከሙት ህመምተኞች መካከል 22% የሚሆኑት የሚሞቱት በወባ በሽታ ምክንያት ነው፣*
- *ለምሳሌ በ1996 (2003) ዓ.ም በተከሰተው በሃገር አቀፍ የወባ በሽታ ወረርሽኝ ምክንያት 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) የሚሆኑት ሰዎች በወባ በሽታ ምክንያት የተጠቁ ሲሆን ከነዚህ መካከል 3,000 የሚሆኑት ሞተዋል:: ይህ ወረርሽኝ የተከሰተው በ3368 አካባቢዎችና በ200 ወረዳዎች ውስጥ ነበር፣*
- *በየዓመቱ ከ4-5 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ በወባ በሽታ ምክንያት ይታመማል:: የተጠናከረ የመረጃ አሰባሰብ ቢኖር ግን የሕሙማን ቁጥር እስከ 10,000,000 ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል::*

**5. የወባ በሽታ የወደፊቱ ስጋት**

- *የወባ በሽታ ከሚያስከትለው የጤና ፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የመከላከል እርምጃ ያለመወሰድ፣*
- *የጤና አገልግሎት ሽፋን አናሳ መሆኑ ቢታወቅም በአሆኑ ጊዜ እስከ 70% ማደጉ ቢታወቅም፣*
- *ሕብረተሰቡ በጤና አገልግሎት የመጠቀም ሁኔታው እጅግ በጣም አናሳ በመሆኑ፣*
- *ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር በተለይም በትንኝ ጥናትና ቁጥጥር በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለመኖር፣*
- *የወባ አስተላላፊ ትንኞች ለጸረ ትንኝ መድኃኒት ያለመበገር*
- *የኢኮኖሚ ወይም ያለውን ሃብት በአግባቡ የመጠቀም ችግር*
- *ሊተነበይ የማይችል የአየር ጠባይ፣ የስነምህዳርና የአካባቢ መለወጥ ለወባ አስተላላፊ ትንኞች መራባት እና ለበሽታው ተህዋሲያን መተላለፍ ከምንጊዜው የበለጠ አመቺ በመሆኑ፣ (ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብና መጠነ ሠፊ የጐርፍ አደጋ በየአካባቢው መከሰት፣ ወዘተ)፣*
- *በሠፈራና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች የወባ በሽታን የመቋቋም አቅሙ ዝቅተኛ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል በብዛት ከደጋማው ወደ ቆላማው ክፍል ለሥራ ፍለጋ መንቀሳቀስ፣*
- *የአነስተኛና የሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች በየአካባቢው መስፋፋት፣*
- *የውሃ ማቆር ኘሮግራም በየአካባቢው መስፋፋት፣*
- *የመስክ የወባ ሥራን ለማካሄድ የተጠናከረ አመራር፣ የትራንስፖርት ችግር መኖር፣*

- የሙያ ማህበራትንና ሌሎችን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በአግባቡ ማሳተፍ ያለመቻል፣
- የምግብ ማነስና ያለመመጣጠን ወይም የረሃብ ችግር፣
- የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝ መከሰት፣ በሳንባ ነቀርሳ መስፋፋትና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች ህብረተሰቡ የወባ በሽታን ለመቋቋም ያለው የተፈጥሮ አቅም እየተዳከመ ስለሚሄድ የወባ በሽታ ለወደፊቱ አመርቂ የቁጥጥር እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር የበሽታው ጥቃት እየተባባሰ እንጂ እየተሻሻለ አይመጣም::

## *5.1 በአሁኑ ጊዜ የወባ በሽታን ለመከላከል እየወተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች*

የወባ በሽታ እያስከተለ ካለው የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጫና ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የወባ በሽታን የመቆጣጠር ወይም የመከላከል እርምጃ እየተወሰደ ነው ባይባልም:-

- አጠቃላይ የጤና አገልግሎቱን ለማራመድ የጤና ፖሊሲ ወጥቷል፣
- እያንዳንዱ ክልል የራሱ የሆነ የአፈጻጸም ስልት በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገ ነው፣
- የአምስት አመት ኘላን ተዘጋጅቷል
- ግሎባል ፈንድን ጨምሮ ከፍተኛ የውጭ እርዳታ አለ፣
- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት ለመከላከሉ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፣
- ይሁን እንጂ ከነባራዊ ሁኔታዎች እንደምንመለከተው የወባ በሽታ ችግር እምብዛም ሊቀረፍ አልቻለም::

## *5.2 ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች*

አብይ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍ:-

- ከየክልሉ ወጣት ተማሪዎች ተመልምለው በወባ በሽታ ቁጥጥር ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች በወባ በሽታ ላይ የምርምር ጥናት እንዲያደርጉ ማበረታታት፣
- የወባ በሽታ ቁጥጥር የሥራ እንቅስቃሴ በዋና መ/ቤትና በክልሎች ደረጃ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ ከፍተኛ ባለሙያዎች በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር እንዲሰለጥኑ ማድረግ፣
- ከተቻለ በመንግሥትና በግል የጤና ተቋማት፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ዩኒቨርስቲዎች ስለወባ በሽታ ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ማድረግ፣

- በዋና መ/ቤትም ሆነ በክልሎች ደረጃ የተጠናከረ የአስተዳደር መዋቅር እንዲኖረው ማድረግ፣
- መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እየተካሄደ ባለው የወባ ቁጥጥር ሥራ ተገቢውን ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

## 6. የኢትዮጵያ የወባ መቆጣጠሪያ ባለሙያዎች ማኅበር መቋቋም

*የኢትዮጵያ የወባ መቆጣጠሪያ ባለሙያዎች ማኅበር መንግሥታዊ ያልሆነ የፖለቲካ አመለካከት የሌለውና ለትርፍ ያልተቋቋመ የሙያ ማኅበር ነው፡፡ ማኅበሩ በቀድሞው የወባ ማጥፊያ ባለሙያዎች መሥራች አባልነት ከሰኔ 21 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ ከፍትህ ሚኒስቴር ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ በይፋ የተቋቋመ ነው፡፡*

*የማኅበሩ ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረገው አገር አቀፍ እንቅስቃሴ በአጋርነት በመሰለፍ የወባ በሽታ የኅብረተሰቡ ዓብይ የጤና፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ችግር እንዳይሆን የበኩሉን ጥረት ማድረግ ነው፡፡*

*የማኅበሩ ዋና ርዕይ የወባ በሽታ በኢትዮጵያ ውስጥ እያደረሰ ያለውን ጫና ለመቀነስና የኅብረተሰቡ ዓቢይ የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግር እንዳይሆን ለማድረግ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የወባ በሽታ ከድህነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በወባማ አካባቢዎች ያለውን የድህነትና የወባ በሽታን የዑደት ቁርኝት እንዲቋረጥ ማድረግ ነው፡፡*

*የማኅበሩ ተልዕኮ፡- የወባ በሽታን በአመርቂ ሁኔታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የተቀናጀ መንደር አቀፍ የወባ በሽታ ቁጥጥር ስልት ለመቀየስ የሚያስችል ፕሮጀክት በሃገር አቀፍ ደረጃ ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡*

### ዋና ዓላማ

*የማኅበሩ ዋና ዓላማ የወባ በሽታ ከእንግዲህ ዓቢይ የኅብረተሰብ የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ችግር እንዳይሆን በወባ በሽታ ምክንያት የሚከሰተውን የህመም ስቃይና የሞት መጠን ለመቀነስ በሚደረገው ርብርቦሽ የበኩሉን ሙያዊ አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው፡፡*

### ማኅበሩ የሚያከናውናቸው ልዩ ልዩ ተግባራት

*ማኅበሩ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባወጣው የጤና ፖሊሲና የክልል ጤና ቢሮዎች የሚቀርጿቸውን የሥራ አፈጻጸም ሥልቶች በመከተል በወባ በሽታ ላይ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ በየጤና ድርጅቱ ለሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች የወባ በሽታ ስለሚያስከትላቸው የጤና፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውሶች*

ተገቢውን ቅስቀሳና ሥልጠና በመስጠት የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ግንዛቤያቸውን በማዳበር ይህን ዘመን ያስቆጠረ ዓብይ የጤና ችግር ለመቅረፍ የሙያ ድጋፍ መስጠት ነው።

ከሁሉም በላይ የወባ በሽታን በአግባቡ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንቅፋት ከሆኑት በርካታ ግንባር ቀደም ምክንያቶች መካከል በሙያ መስኩ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ነው። ይህን ችግር ለመቅረፍ ማህበሩ በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚቻልባቸውን ሥልቶች ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርንና የክልል ጤና ቢሮዎችን ጨምሮ ከሌሎች አጋሮችና ተቆርቋሪዎች ጋር በመሆን በሃገር አቀፍ ደረጃ ችግሩ የሚቃለልበትን ዘዴ ለመሻት ድምጹን ከፍ አድርጎ በማሰማት የበኩሉን የሙያ አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው።

## የማህበሩ አባል ስለመሆን

የማኀበሩ አባል ለመሆንና ከጎናችን የሚቆሙ ወገኖች ሁሉ የማኀበሩን ዓላማዎችና ግቦች ለመቀበል ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግል ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ፍላጐት ያላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች ሁሉ የማኀበሩ አባል ሊሆኑ ይችላሉ።

ማኅበሩ በአሁኑ ወቅት የወባ በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ዘርፈ ብዙ እውቀት ያላቸውና የወባ በሽታን ጨምሮ በተለይም በጤና አጠባበቅ ዙሪያ ከፍተኛ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ኤክስፐርቶች አሉት። አብዛኛዎቹ አባላት ከቀድሞው የኢትዮጵያ ወባ ማጥፊያ ማሠልጠኛ ተቋም የተመረቁና የወባ በሽታን በማጥፋትና በመከላከል ረገድ ለረጅም ጊዜ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉና በሙያ መስኩ በቂ የሥራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው።

# FSS Publications List

**[currently available in stock]**

| FSS Periodical |
|---|
| • *Medrek, now renamed FSS BULLETIN* (Quarterly since 1998. English and Amharic) |
| • *Africa Review of Books* (Managed by FSS for CODESRIA)<br>o Vol. 1, No. 1 (October 2004)<br>o Vol. 1, No. 2 (September 2005)<br>o Vol. 2, No. 1 (March 2006)<br>o Vol. 2, No. 2 (September 2006) |

| | FSS Discussion Papers | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 5 | *Land Redistribution and Female-Headed Households: A Study in Two Rural Communities in Northwest Ethiopia.* Yigremew Adal. 2001 | 20.00 |
| No. 8 | *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. 2002 | 20.00 |
| No. 9 | *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. 2002 | 20.00 |
| No.10 | *Rural Lands and Evolving Tenure Arrangements in Ethiopia: Issues, Evidences and Policies.* Tesfaye Teklu. 2003 | 20.00 |
| No.11 | *Resettlement in Ethiopia: The Tragedy of Population Relocation in the 1980s.* Dessalegn Rahmato. 2003 | 20.00 |
| No.12 | *Searching for Tenure Security? The Land System and New Policy Initiatives in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato. 2004 | 20.00 |
| No.13 | *A Comparative Study of Forest Management in Eza District, Gurage Zone, Southern Ethiopia.* Tenkir Bonger. 2005 | 20.00 |

| | FSS Monograph Series | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 2 | *Poverty And The Social Context of Sex Work In Addis Ababa: An Anthropological Perspective.* Bethlehem Tekola. 2006 | 40.00 |
| No. 3 | *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004 | 25.00 |
| No. 4 | *Lord, Zega and Peasant: A Study of Property and Agrarian Relations in Rural Eastern Gojjam.* Habtamu Mengistie. *2004* | 30.00 |

| | Consultation Papers on Poverty | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 3 | *Civil Society Groups and Poverty Reduction.* Abonesh H. Mariam, | 5.00 |

| | | |
|---|---|---|
| | Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. 2001 | |
| No. 4 | *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse (in Amharic). Edited by Meheret Ayenew. 2001 | 5.00 |

| **Gender Policy Dialogue Series** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 1 | *Gender and Economic Policy.* Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 2 | *Gender and Poverty* (Amharic). Edited by Zenebework Tadesse. 2003 | 10.00 |
| No. 4 | *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2003 | 10.00 |
| No. 6 | *Gender Policy Dialogue in Southern Region.* Edited by Eshetu Bekele. 2004 | 10.00 |

| **Consultation Papers on Environment** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Environment and Environmental Change in Ethiopia*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Environment, Poverty and Gender.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.3 | *Environmental Conflict*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Economic Development and Its Environmental Impact*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. 2003 | 10.00 |
| No.5 | *Government and Environmental Policy*. Consultation Papers on Environment. 2004 | 10.00 |
| No.6 | *የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)* Consultation Papers on Environment. May 2004 | 10.00 |
| No.7 | *Environmental Challenges of Contemporary Ethiopia and the Indispensable Role of Indigenous Trees*. Legesse Negash. 2004 | 10.00 |

| **FSS Studies on Poverty** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No.1 | *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers.* Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. 2003 | 10.00 |
| No.2 | *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo.* Harald Aspen. 2003 | 15.00 |
| No.3 | *Destitution in Rural Ethiopia.* Yared Amare. 2003 | 10.00 |
| No.4 | *Environment, Poverty and Conflict*. Tesfaye Teklu and Tesfaye Tafesse. 2004 | 10.00 |
| No.5 | *Issues in Urban Poverty: Two Selected Papers*. Daniel Kassahun and Meron Assefa. July 2005 | 10.00 |

| **ከድህነት ወደ ልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ (1ኛ ዙር)**<br>**From Poverty to Development: Intergenerational Transfer of Knowledge (1st Round)** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| **ቁጥር 1** | ***ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)::* ሽመልስ አዱኛ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 2** | ***የአባይና የተፋሰሶቹ ዓለም ዓቀፋዊ ችግር::* ዘውዴ ገ/ሥላሴ፣ 1997 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 2 | *The Blue Nile and Its Basins: An Issue of International Concern.* [English Version]. Zewde G/Sellassie. 2006. | 10.00 |
| **ቁጥር 3** | ***ትምህርት፣ ባህልና ዕድገት: የትዝታ ጉዞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እስከ ዓለም አቀፍ የኤኮኖሚ ተቋማት (1948-1996)::* አስፋው ዳምጤ፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| **ቁጥር 4** | ***ጆርናሊዝምና እድገት በኢትዮጵያ፤ የግል ትዝታዎች ከ1952 ጀምሮ::* ነጋሽ ገ/ማርያም፣ 1998 ዓ.ም.** | 10.00 |
| No. 5 | *National Air Carriers as Catalysts for Development: The Case of Ethiopian Airlines (ET).* Semret Medhane, 2006. | 10.00 |
| **(2st Round)** | | Price (Birr) |
| **ቁጥር 1** | ***አንጋፋው የኢንቨስትመንትና የግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ ተዋናይ::* ተካ ኤገኖ፣ 1999 ዓ.ም.** | 10.00 |

| **Book Series** | Price (Birr) |
|---|---|
| • *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below.* Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Nordic Africa Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2006. Reprint. | 80.00 |
| • *Land and the Challenge of Sustainable Development in Ethiopia.* Edited by Dessalegn Rahmato and Taye Assefa. Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2006. | 75.00 |

| **FSS Research Report** | | Price (Birr) |
|---|---|---|
| No. 1 | *Rainwater Harvesting in Ethiopia: Capturing the Realities and Exploring Opportunities.* Daniel Kassahun. Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2007. | 25.00 |

| **Environmental Documentaries on CD and Video** | Price (Birr) |
|---|---|
| • የከተማችን አካባቢ ከየት ወደየት? (Amharic Video Film) | 50.00 |
| • ውጥንቅጥ፣ ድህነትና የአካባቢያችን መጎሳቆል (Amharic Video Film) | 50.00 |
| • "Witinkit": Poverty and Environmental Degradation (CD in Amharic with English Subtitles) | 50.00 |

**የማኅበራዊ ጥናት መድረክ**

የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) አትራፊ ያልሆነ፣ ልማት-ነክ በሆኑ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያካሂድ ነፃ ተቋም ነው፡፡ ማጥመ በሕዝባዊ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ነፃ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤ የሕዝብን ግንዛቤ ለማዳበር ይንቀሳቀሳል፡፡ በፖሊሲ ክርክሮች ውስጥ ሰፋ ያለ የሕዝብ ተሳትፎን ማዳበር ለዲሞክራሲው ሂደት ትልቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብሎ ማጥመ ያምናል፡፡ ግቦቹን ለማሳካትም ማጥመ ዐውደ-ጥናቶችን ያዘጋጃል፣ የምርምር ውጤቶቹንም በማሳተም ለፖሊሲ አመንጪዎችና ሌሎች የመንግሥት አካላት፣ ለሲቪል ማኅበራት፣ ለባለሙያዎች፣ ለግሉ ክፍለ-ኤኮኖሚ አባላትና ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ እንዲሁም ለለጋሽ ድርጅቶች ያሠራጫል፡፡

